
የሚኖሩበትን የዋሽንግተን ግዛት

# የHealth Home ቡክሌት

… ለ ተሻለ ህይወት!



ለብቁ ግለሰቦች የሚሆን የHealth Home እንክብካቤ የቅንጅት አገልግሎት

Washington State Department of Social & Health Services
Transforming lives

Washington State Health Care Authority

Washington State Health Care Authority

[English] Language assistance services, including interpreters and translation of printed materials, are available free of charge. Call 1-877-501-2233 (TRS: 711).

[Amharic] የቋንቋ እገዛ አገልግሎት፣ አስተርጓሚ እና የሰነዶችን ትርጉም ጨምሮ በነጻ ይገኛል፡፡ 1-877-501-2233 (TRS: 711) ይደውሉ፡፡

[Arabic] خدمات المساعدة في اللغات، بما في ذلك المترجمين الفوريين وترجمة المواد المطبوعة، متوفرة مجاناً، اتصل على رقم 1-877-501-2233 (TRS: 711).

[Burmese] ဘာသာပြန်ဆိုသူများနှင့် ထုတ်ပြန်ထားသည့် စာရွက်စာတမ်းများဘာသာပြန်ခြင်းအပါအဝင် ဘာသာစကားအထောက်အကူဝန်ဆောင်မှုများကို အခမဲ့ရနိုင်ပါသည်။ 1-877-501-2233 (TRS: 711) ကိုဖုန်းခေါ်ဆိုပါ။

[Cambodian] សេវាជំនួយភាសា រួមមានទាំងអ្នកបកប្រែផ្ទាល់មាត់ និងការបកប្រែឯកសារបោះពុម្ព គឺអាចរកបានដោយឥតគិតថ្លៃ។ ហៅទូរស័ព្ទទៅលេខ 1-877-501-2233 (TRS: 711)។

[Chinese] 免费提供语言协助服务，包括口译员和印制资料翻译。请致电 1-877-501-2233 (TRS: 711)。

[Korean] 통역 서비스와 인쇄 자료 번역을 포함한 언어 지원 서비스를 무료로 이용하실 수 있습니다. 1-877-501-2233 (TRS: 711)번으로 전화하십시오.

[Laotian] ການບໍລິການດ້ານພາສາ, ລວມທັງນາຍແປພາສາ ແລະ ການແປເອກະສານຕີພິມ, ມີໄວ້ໃຫ້ຟຣີໂດຍບໍ່ຄິດຄ່າ. ໂທຫາເລກ 1-877-501-2233 (TRS: 711).

[Oromo] Tajajilli gargaarsa afaanii, nama afaan hiikuu fi ragaalee maxxanfaman hiikuun, kaffaltii malee ni argattu. 1-877-501-2233 (TRS: 711) irratti bilbilaa.

[Persian] خدمات کمک زبانی، از جمله مترجم شفاهی و ترجمه اسناد و مدارک (مطالب) چاپی، بصورت رایگان ارائه خواهد شد.با شماره 1-877-501-2233 (TRS: 711) تماس بگیرید.

[Punjabi] ਭਾਸ਼ਾ ਸਹਾਇਤਾ ਸੇਵਾਵਾਂ—ਦੁਭਾਸ਼ੀਏ ਅਤੇ ਪ੍ਰਿੰਟ ਕੀਤੀ ਹੋਈ ਸਮੱਗਰੀ ਦੇ ਅੰਨੁਵਾਦ ਸਮੇਤ—ਮੁਫ਼ਤ ਉਪਲੱਬਧ ਹਨ। 1-877-501-2233 (TRS: 711) 'ਤੇ ਕਾਲ ਕਰੋ।

[Romanian] Serviciile de asistență lingvistică, inclusiv cele de interpretariat și de traducere a materialelor imprimate, sunt disponibile gratuit. Apelați 1-877-501-2233 (TRS: 711).

[Russian] Языковая поддержка, в том числе услуги переводчиков и перевод печатных материалов, доступна бесплатно. Позвоните по номеру 1-877-501-2233 (TRS: 711).

[Somali] Adeego caawimaad luuqada ah, ay ku jirto turjubaano afka ah iyo turjumid lagu sameeyo waraaqaha la daabaco, ayaa lagu helayaa lacag la'aan. Wac 1-877-501-2233 (TRS: 711).

[Spanish] Hay servicios de asistencia con idiomas, incluyendo intérpretes y traducción de materiales impresos, disponibles sin costo. Llame al 1-877-501-2233 (TRS: 711).

[Swahili] Huduma za msaada wa lugha, ikiwa ni pamoja na wakalimani na tafsiri ya nyaraka zilizochapishwa, zinapatikana bure bila ya malipo. Piga 1-877-501-2233 (TRS: 711).

[Tagalog] Mga serbisyong tulong sa wika, kabilang ang mga tagapagsalin at pagsasalin ng nakalimbag na mga kagamitan, ay magagamit ng walang bayad. Tumawag sa 1-877-501-2233 (TRS: 711).

[Tigrigna] ተርጎምትን ናይ ዝተፅሓፉ ማተርያላት ትርጉምን ሓዊሱ ናይ ቋንቋ ሓገዝ ግልጋሎት፤ ብዘይ ምንም ክፍሊት ይርከቡ፡፡ ብ 1-877-501-2233 (TRS: 711) ደውሉ፡፡

[Ukrainian] Мовна підтримка, у тому числі послуги перекладачів та переклад друкованих матеріалів, доступна безкоштовно. Зателефонуйте за номером 1-877-501-2233 (TRS: 711).

[Vietnamese] Các dịch vụ trợ giúp ngôn ngữ, bao gồm thông dịch viên và bản dịch tài liệu in, hiện có miễn phí. Gọi 1-877-501-2233 (TRS: 711).

# የሚኖሩበትን የዋሽንግተን ግዛት
# የHealth Home ቡክሌት

## Health Home ምንድን ነው?

Health Home ቦታ አይደለም፤ በአንድ ላይ ተቀናጅቶ የሚሰራ የእንክብካቤ አገልግሎት ነው። ይህ አገልግሎት የሚሰጠው በአንድ የእንክብካቤ አቀናጅ ሲሆን ይህ ግለሰብ በአሁኑ ሰዓት እርስዎ ከሚያገኙትን አገልግሎት እና ድጋፍ ጥቅም እንዲያገኙ የሚረዳዎት ሰው ነው።

Health Home የሚሰጣቸው አገልግሎቶች በቀጣይ ከሚያምዎት በሽታ ጋር በሚጋፈጡበት ወቅት የሚደግፍዎ እና የመረጡትን የጤና ግብ ላይ እንዲደርሱ የሚያግዝዎት አገልግሎት ነው። የHealth Home አገልግሎቶች በሕክምናው እና በማሕበራዊ ጉዳዮች ላይ የሚያስፈልጉትን ነገሮች በማቀናጀት ረገድ ማሻሻያ ያመጣል፣ ይህም ለረዥም ጊዜ የሚቆዩ አገልግሎቶችና ድጋፎችን እንዲሁም መድሐኒት የሚያስፈልጋቸው ሕመሞችን ጨምሮ በአጠቃላይ የፀባይ ጤናን የሚያካትት ነው። የHealth Home መርሐ ግብር የሚያገኙትን እንክብካቤ ይበልጥ ተደራሽነት እንዲኖረውና የተቀናጀ እንዲሆን ይረዳል።



## የHealth Home አገልግሎቶች ምንድን ናቸው? እርስዎን ሊረዳዎት የሚችለውስ እንዴት ነው?

- አጠቃላይ የእንክብካቤ ማኔጅመንት ሲባል በግለሰብ ደረጃ የሚሰጥ የጤና መርሐ ግብር ግቦችን የሚያካትት ሆኖ እነዚያን ግቦች ለማሳካት የሚያስችሉ እርምጃዎችን የሚያጠቃልል ነው።
- የእንክብካቤ ቅንጅት መኖሩ ከአገልግሎት ሰጪዎ፤ ከቤተሰብዎ፤ እንዲሁም ከሌሎች እንክብካቤ ሰጪዎች ጋር የተሻለ ሐሳብ ለሐሳብ የመለዋወጥ መስመር እንዲኖር ያደርጋል።
- የሽግግር መርሐ ግብር ደግሞ ከሆስፒታል ወይም ከእንክብካቤ ማዕከል ሲወጡ ሊረዳዎት ይችላል።
- በግለሰብ እና በቤተሰብ ደረጃ የሚሰጡ የድጋፍ አገልግሎቶች፤ የጤና ግብዎ ላይ ለመድረስ ጥረት በሚያደርጉበት ወቅት የቤተሰብዎ አባላት፥ በተዘዋዋሪ ድጋፍ የሚደርጉትን፥እንዲሁም እንክብካቤ ሰጪዎች ያላቸውን ሚና ይለያል።
- ወደ ማሕበረሰብ እና ወደ ማሕበረሰብ ድጋፍ አገልግሎቶች የሚደረጉ ሪፈራሎች፥ እንደ መጓጓዣ፥ ምግብ እና ቤት ከመሳሰሉት ነገሮች በተያይዘ ሊረዱ ይችላሉ።
- የጤና ማስታወቂያ የጤና ግብዎ ላይ እንዲደርሱ የሚረዳዎትን ትምህርትና የጤና መመሪያ እንዲያገኙ ሊያግዝዎት ይችላል።

## የHealth Home አገልግሎቶችን ለማግኘት ብቁ ሊሆን የሚችለው ማን ነው?

ይህንን የHealth Home ቡክሌት የተቀበሉት ለመርሐ ግብሩ ብቁ ስለሆኑ ነው። አገልግሎቱ የሚሰጠው በማንኛው ዕድሜ ለሚገኝና ቢያንስ ብቁ ሊያደርገው የሚችል የረዥም ጊዜ በሽታ ላለው ግለሰብ ነው። አንድን ሰው ብቁ ሊያደርገው ከሚችለው የረዥም ጊዜ በሽታ የሚቀጥሉትን ይገኙበታል:-

- ካንሰር
- ከባድ የመተንፈሻ አካላት ሕመም
- የአእምሮ ሕመም ወይ የመርሳት (አልዛይመርስ) በሽታ
- የስኳር በሽታ
- በጨጓራ ሕመም
- የልብ ሕመም
- የአእምሮ ሕመም
- የፀባይ ጤና እክል
- የጡንቻና አጥንት ሕመም
- የነርቭ ሕመም

## የHealth Home እንክብካቤ አስተባባሪ ሲባል ምንድን ነው?

የHealth Home እንክብካቤ አስተባባሪ በHealth Home መርሐ ግብር ላይ እንዲካፈሉ የሚረዳዎት ግለሰብ ነው። ይህ የእንክብካቤ አስተባባሪ በትክክለኛው ግዜና ቦታ ከትክክለኛው አገልግሎት ሰጪ ትክክለኛው እንክብካቤ እንዲያገኙ አብሮት በመሆን ይሰራል።

ይህ የእንክብካቤ አስተባባሪ የእንክብካቤ ቅንጅት አገልግሎቱን ለመግለፅ እንዲሁም ስለ Health Home መርሐ ግብር ያለዎትን ማንኛውንም ጥያቄ ለመመለስ ከእርስዎ ጋር ይገናኛል።

## የHealth Home አገልግሎት የሚያገኙት እንዴት ነው?

የHealth Home መርሐ ግብር ላይ ለመመዝገብ ሶስት መሰረታዊ እርምጃዎች አሉ:-

**1. ወደ Health Home መመደብ ይኖርብዎታል:-** ብቁ የሆኑ ጊዜ በHealth Home ከሚመራ ድርጅት ጋር ይገናኛሉ፤ ድርጅቱም ከእርስዎ ጋር የሚገናኝ የእንክብካቤ አስተባባሪ ይመድብልዎታል። የእንክብካቤ አስተባባሪው ያለዎትን ጥያቄ ይመልስልዎታል፤ ከዛ በኋላ በHealth Home መርሐ ግብሩ ላይ መካፈል ይፈልጉ እንደሆነ መወሰን ይችላሉ።

**2. *መረጃ የማካፈልና የስምምነት ቅፅመሙላት ይኖርብዎታል:-*** የእንክብካቤ አስተባባሪው ይህንን የHealth Home አገልግሎት ስምምነት ቅፅ እንዲሞሉ ሊረዳዎት ይችላል፤ ይህም የሕክምና እና የማሕበራዊ አገልግሎት መረጃዎትን እንዲያካፍሉ ያስችልዎታል። መረጃው ለአገልግሎት ሰጪዎች እና እርስዎ ለሚመርጧቸው ሰዎች ብቻ ነው የሚሰጠው።

**3. የHealth Action መርሐ ግብሩን መሙላት:-** የራስዎን የጤና ግብ መምረጥ ስለሚችሉ፤ የእንክብካቤው አስተባባሪ ይህንን በራስዎ የHealth Action መርሐ ግብር ላይ ያካትተዋል። ይህ ደግሞ እርስዎ እና የእንክብካቤ አስተባባሪው ከተሚከተሉት በተጨማሪ ሌላ አገልግሎት እና እገዛ ያስፈልግዎት እንደሆን ለማወቅ አገልግሎቶች፣ እንደ:

- በጤና እንክብካቤ ረገድ የሚያስፈልግዎት ነገር
- የረዥም ጊዜ አገልግሎትና ድጋፍ
- የባህሪያዊ ጤና አገልግሎቶች
- የማሕበረሰብ እገዛ
  - ቤት
  - መጓጓዣ

በመጪው ጊዜ በማንኛውም ሰዓትና በመረጡት ሁኔታ ስር ጉብኝት እንዲያደርጉ መጠየቅ ይችላሉ።

## በአሁኑ ሰዓት የጤና እንክብካቤ እና ሌላ አገልግሎት ከሚሰጥዎ ጋር መቆየት ይችላሉ?

አዎን፤ በአሁኑ ሰዓት የጤና እንክብካቤ እና ሌላ አገልግሎት ከሚሰጡት ጋር ይቆያሉ። የHealth Home አገልግሎቶች ከሚያካትተው ነገር አንዱ፤ የእንክብካቤ አስተባባሪው እርስዎ የሚያስፈልግዎ ነገር ሲቀየር የሚያገኙትን የጤና ሽፋን እና ሽግግር ጥሩ እንዲሆን ያስችል ዘንድ ከአገልግሎት ሰጪዎች ጋር የሚያደርገው ግንኙነት ነው።

## አገልግሎት ሰጪዎች በHealth Home መርሐ ግብር ላይ እንደተመዘገቡና ከማን ጋር መገናኘት እንዳለባቸው የሚያውቁት እንዴት ነው?

ProviderOne የሚባለውን በማየት ሊያውቁ ይችላሉ ወይም ወደ 1-800-562-3022 ደውለው ከጤና እንክብካቤ ባለስልጣን ጋር በመገናኘት ሊያውቁ ይችላሉ።

## ለHealth Home አገልግሎቶች መክፈል ያስፈልግዎታል?

አይ አያስፈልግዎትም፤ እነዚህን አገልግሎቶች በነፃ ነው የሚሰጡት።

### በእንክብካቤ አስተባባሪው ካልተደሰቱስ?

ከHealth Home የእንክብካቤ አስተባባሪው ድርጅት ጋር በመገናኘት ሌላ የእንክብካቤ አስተባባሪ እንዲመደብልዎ ሊጠይቁ ይችላሉ።

### በግዛቱ ውስጥ ወደሚገኝ ሌላ ቦታ ከተዘዋወሩስ?

አዲስ የእንክብካቤ አስተባባሪ ሊመደብልዎ ይችላል። ስለ ቀጣይ አገልግሎቶቹ ለመነጋገር ተገናኝነው ይወያይበታል።

## የApple Health (Medicaid) ወይም የMedicare ሽፋንዎ ከጠፋስ?

የApple Health (Medicaid) ብቁነትዎ ከጠፋ፣ ለHealth Home አገልግሎት ብቁ መሆንዎንም ያቋርጣል።

የMedicare ብቁነትዎ ከጠፋ፣ የApple Health (Medicaid) ብቁነትዎ ግን ካልጠፋ፣ ለHealth Home አገልግሎቶች ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ።

### ቅሬታ የማቅረብና የይግባኝ መብትዎ በተመለከተስ?

አሁን ያለዎትን የApple Health እና የMedicare ቅሬታ የማቅረብ እና የይግባኝ መብትዎ እንደተጠበቀ ይቀጥላል።

## በHealth Home መርሐ ግብር ላይ መቀጠል ካልፈለጉስ?

ከHealth Home እንክብካቤ አስተባባሪው ጋር በመነጋገር ከመርሐ ግብሩ እንዲያስወጣዎት ሊነግሩት ይችላሉ። ከጊዜ በኋላ ሐሳብዎ ከቀየሩ፣ ወደ 1-800-562-3022 ደውለው ከጤና እንክብካቤ ባለስልጣን ጋር በመገናኘት ወደ Health Home መርሐ ግብር እንደገና እንዲመዘገቡ መጠየቅ ይችላሉ።

### ለ አመሪካውያን ሕንዶች ወይም አላስካ ተወላጆች

ብቁ የሆኑ አመሪካውያን ሕንዶች ወይም ተወላጆች በማንኛውም ጊዜ በHealth Home ለመካፈል ሊመርጡ ይችላሉ፤ ይህም የሚያደርጉት ከጤና እንክብካቤ ባለስልጣን ጋር በመገናኘት ሊያደርጉት ይችላሉ፥ ባለስልጣኑም ብቃታቸውን በማረጋገጥ በምዝገባው ሂደት ላይ ሊረዳቸው ይችላል።



## በ ጤና ችግር ጊዜ ወደማን መደወል እንደሚችሉ

ለሕይወት አስጊ የሆነ ችግር ሲያጋጥም ወደ

# 911 ይደውሉ።

### ኢንተርኔት ላይ

ስለ Health Home መርሐ ግብር ይበልጥ ማወቅ ከፈለጉ ይህንን ድረገፅ ይጎብኙ፦**hca.wa.gov/free-or-low-cost-health-care/apple-health-medicaid-coverage/health-home**።

HCA በሚሰጠው አገልግሎት ረገድ እኩልነት እንዲፀባረቅ በትጋት ይሠራል። ለጊዜው የሚቆዩበትን ቦታ ከፈለጉ ወይም ሰነዱን በሌላ ፎርማት ማግኘት ከፈለጉ እባክዎትን ወደ 1-800-562-3022 ይደውሉ። መስማት ወይም መናገር የተሳናቸው ሰዎች ካሉ ወደ 711 በመደወል የሚፈልጉትን አገልግሎት ማግኘት ይችላሉ።

P.O. Box 45535
Olympia, WA 98504-5535

HCA 22-851 AM (6/21) Amharic